*<u>ወይ ጥጋብ ወይ ጥጋብ (ተስፋሁን ሞላ)</u>*

ወይ ጥጋብ ወይ ጥጋብ በእብሪት መወጠር

ተከዜን ተሻግሮ ፈለገ የቀኝ ግዛት ሀገር

ወያኔ አፉን ሞልቶ አለ የእኔ ነው ጎንደር።

ታቦት ተሸክመው ተው ግደፍ እያሉ ቢለግሱት ምክር

አሻፈረኝ ብሎ ሰሮቃ ላይ ደርሶ ቁሞ ሲፎክር

ድንገት ሳያስበው ከአንገቱ ቆመበት የአርማጭሆ ነብር።

የነብር ልጅ ነብር የአንበሳም አንበሳ

በድምጹ ያስፈራል ተነስቶ ሲያገሳ።

የዝንጀሮ መንጋ እንዴት ቢደፍር ነው

ከነብሮቹ ሰፍፈር ሊገባ ያማረው

ከአንበሶቹ ቦታ ሊገባ ያሰበው

አንገት ቢደፉ የሞቱን መሰለው።

የመቅደላው ተዶ የቋራው አንበሳ

በየቦታው ሁሉ የሱሰም ሲነሳ

አገሬው በሙሉ ሊዘምት ተነሳ።

የጠፋውን ታሪክ መልሶ ሊያድስ

ወሰኔ ነው አለ ተከዜ ድረስ

ደበሬ ነው አለ ከወንዙ መለስ።

ታቦት ተሸክመው ቢለምኑት አሻፈረኝ ያለው

ተመልሶ ሄደ ምክንያት ሳይኖረው

የአንበሶችን ክንድ መቋቋም ሲያቅተው።

ስለ ፈረጠጠ ወያኔን አትመን

ቁጭ ብሎ ይጠብቃል እስከ ምትበተን።

አንዴ ጀምረሃል ግፋ ወደ ፊት

ተከዜን አሻግረው ቆልተህ በጥይት።

ለትግራይ ሕዝብ አለኝ የማስተላልፈው
አንተም ተቀብለህ መቀመጫ ንሳው
ሊያጣላህ ተነስቶአል ከጎንደር ሕዝብ ጋር አብረህ ከምትበላው
ሊያፋጅህ ተነስቶአል ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር አብረህ ከምትኖረው።

በአንተ እየነገደ እድሜው እንዳይረዝም
ከወገን ጋራ ሁነህ ዝመትበት አንተም።
እሱ ነገ ያልፋል አጭር ነው እድሜው
አንተነህ የምትኖር እስከ ወዳኛው።

አባትየው ሲያልፍ ልጁ እየተተካ፤
ዘለዓለም እንዳይኖር ቁስሉ እየተነካ፤
የሰው ሁሉ ቁስል ለአንተም እንዳይተርፍህ፤
እንዲሽር አድርገው በተሎው አፍርጠህ።
በእሱ የተነሳ እንዳያገኝህ መከራና ችግር
የፋሽስት ሎሌ ይህ የባአንዳ ዘር
ከአንተ ጉያ ሆኖ እንዳይውል እንዳያድር
አሁን ተነሳበት አብረህ ከወገን ጋር
ተባብረህ አሳደው እድሜው እንዲያጥር።

የጎነደር ህመም ለጎጃም ሲሰማው
የጎጃምም ቁስል ለጎንደር ሲሰማው
ጠላትን ለማጥፋት በአንድ ላይ ተባብረው
ጀምረዋል አሁን እጅ እና ጓንት ሁነው።
ወሎም ተነስ በዚያ ለሸዋም ንገረው
ባአንዳውን ሰብስቦ ጉድጓድ እንዲያስምሰው።

የተናገረው ቃል መቼም አይረሳህ
አማራን አልቀበርነውም -ጂ ገለነዋል ያለህ።

ትናአት ባሕር ዳር ላይ የተሳለቀብህ

መቼም አይረሳ ሲወሳ ይኖራል እስከ ልጅ ልጅህ።

ጎጃም ላይ ሲያካፋ ጎንደር ላይ ይዘንባል

መጉረፉም አይቀር  አንዴ ጀምሮታአል።

የደፈረሰው እስኪ ጠራ ድረስ

አባይን በታንኳ ተከዜን በፈረስ

አሻገረህ ስደደው ዞሮ እንዳይመለስ።

ኢትዮጵያ ተከብራ ለዘላዓለም ትኑር

በልጆቿ አንድነት በሁሉም ትብብር

ዳር ደበሯ ሁሉ ወሰኗ ይከበር።

ታሕሣሥ ፳፬ ቀን፡፪ሺ፲፭፤ ዓ/ም (02/01/2015)